# ጽርሐ አርያም

ተመየጡ ፡ ኀቤየ ፡ በኵሉ ፡ ልብክሙ ፡ በጾም ፡ በላሕ ፡ ወበብካይ (ኢዩ ፪፥፲፪)　　በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ (ኢዩ ፪፥፲፪)

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል**
**2601 Minnehaha Ave, Minneapolis, MN 55406 Tel: 612-913-7000**

**ሰኔ ፳፻፰ ዓ.ም/ቅጽ፩/ቁጥር ፫　　ወርኃዊ ጋዜጣ　　July 2016/Volume 1/Issue 3**


## "ከጾሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቷቸው " ሐዋ ፲፫፥፫

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።አሜን።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ከተለያየ የኑሮ ጠባይና የሥራ መስኮቻቸው ላይ ሲጠራቸውና የተአምራቱ ተቋዳሽ፣ የምሥጢሩ ተካፋይ አድርጎ ሲያከብራቸው ወደፊት ስለሚሸከሙት ታላቅ አደራ እሱ ባወቀ እያዘጋጃቸው ነበረ። የጥሪውን ነገር በዕለተ አርብ በድንግዝግዝ ቢረዱትም ከትንሣኤው በኋላ ግን ከዛ በፊት ያልተረዱትን የአገልግሎት ጥሪ ታላቅነት በግልፅ እያዩት መጡ። ከእግሩ ሥር ተቀምጠው የተማሩትን ትምህርት በሥራ ላይ የሚያውሉበት ዘመን መቅረቡን ተረዱ። ከማረጉም በፊት አፅናኝ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ እንደሚልክላቸው እና ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች እንደማይተዋቸው ቃል ገብቶ ሲለያቸው የዛ ሁሉ ዘመን ዝግጅት እስከሞት ድረስ የሚደርስ ቆራጥነት የሚጠይቅ ኃላፊነት መሆኑን ተረድተውና ከመንፈስቅዱስ አጋዥነት ጋር የሚገጥማቸውን ፈተና እንደሚያልፉት አምነው ነው ሊያገለግሉት የተነሱት። ወደየሀገረ ስብከታቸው ከመሰማራታቸው በፊት ግን በፆም እና በጸሎት ለታመነ አምላክ ራሳቸውን አደራ ሰጡና ይኸው ከምዕተ ዓመታት ብዛት ነዶ የማያልቅ የአገልግሎት ጧፍ ሆነውና ለኩሰው ተጠሩ። በሐዋርያት እግር የተተኩ አባቶቻችንም ፆመ ሐዋርያት ብለን የምንፆመውን ፆም ከአዋጅ አፅዋማት አንዱ አድርገው ልጆቻቸው እንፆመው ዘንድ ሥርዓት ሠሩልን። ፆመ ሐዋርያት ከበዓለ ጰራቅሊጦስ እሑድ ማግስት ጀምሮ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ የተሰዉበትን ዕለት እስከምናከብርበት ሐምሌ ፭ ድረስ የሚፆም ሲሆን ለመፆም ዕድሜያቸው የደረሱ በሙሉ ይፆሙት ዘንድ የታዘዘ ነው። ሐዋርያት ይኼን ዓለም ከመጋፈጣቸው በፊት በፆም እንደተዘጋጁ እኛም ሥራችንን ሁሉ በፆም በፀሎት እንጀምረው ዘንድ ይገባል። ቀሪዎቹን የፆመ ሐዋርያት ሳምንታት በትጋት ሆነን እንድንፈፅም እና ከቅዱሳን ሐዋርያት ረድኤት በረከት እንዲከፍለን የአምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣ ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!*

*በሰብለወንጌል ደምሴ*

**ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ት/ቤት**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ት/ቤት የተመሠረተበትን ታሪካዊ ፳ኛ ዓመታዊ በዓሉን በተለያዩ መንፈሳዊ ዝግጅቶች ከቤተ ክርስቲያናችን እና ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ተጋብዘው ከሚመጡ ካህናት ጋር በመሆን ለማክበር ተዘጋጅቷል።

ቦታ፡ ርእሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል (2601 Minnehaha Ave. Minneapolis, MN 55406)

መቼ፡ ከአርብ ሐምሌ ፲፭ እስከ እሑድ ሐምሌ ፲፯/፳፻፰ ዓ.ም. (July 22-24, 2016)

በመርሐ ግብሩ ከሚካተቱት የትምህርት፣ የመዝሙር፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ የዐውደ ርእይ እና የመሳሰሉት በርካታ ዝግጅቶች መካከል እሑድ ሐምሌ ፲፯/፳፻፰ ዓ.ም. (July 24, 2016) "**የኢዮብ መከራ እና የእግዚአብሔር ቸርነት**" በሚል ርእስ የተዘጋጀ ተውኔት ይቀርባል።

*በቤተ ክርስቲያናችን ድረ ገጽ ላይ ጋዜጣችንን ለማንበብ፡- www.minnesotaselassie.org/newsletter/*
*አስተያየት ለመስጠት ወይም ጥያቄ ካለዎት ኢሜላችን (email) ፡- newsletter@minnesotaselassie.org*

## ማውጫ


| ዝርዝር | ገጽ |
|---|---|
| 1. ከጾሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው | 1 |
| 2. ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ት/ቤት | 1 |
| 3. ትምህርተ ሃይማኖት ፡ - አምስቱ አእማደ ምስጢር (ክፍል 1) | 2 |
| 4. ነገረ ቅዱሳን፡ - ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ፤ | 3 |
| 5. የተባረከ ቤተሰብ | 4 |
| 6. የሕፃናት እና ወጣቶች ዓምድ - Enter Through the Narrow Gate | 5 |
| 7. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጥያቄ እና መልስ፡ - መቋሚያ | 6 |
| 8. ቅዱሳት ሰዕላት | 7 |
| 9. ጠቃሚ መረጃዎች | 8 |



**እዘጋጆች**

ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ
ዶ/ር ሰሎሞን ፎሌ
ወ/ሮ ሰብለወንጌል ደምሴ
ወ/ት ዘመናይ ዘሪሁን
አቶ አብርሃም ሰሎሞን

**አርታእያን**

መልአከ አርያም ቆሞስ አባ ኃይለሚካኤል ሙላት
ሊቀ ብርሃናት ቀሲስ ሄኖክ ያሬድ

**ዲዛይን**

አቶ ውብሸት አየለ
ዶ/ር ሰሎሞን ፎሌ

# ትምህርተ ሃይማኖት

## አምስቱ አዕማደ ምሥጢር (ክፍል ፣)

አምድ ማለት ምሰሶ ማለት ሲሆን በቁሙ ስንገልጽው የአንድ ቤት ጣሪያ ወይም የቤቱ ምሰሶ ብለን የምንጠራው እና ቤቱ እንዳይዘም ወይም ወደ አንድ ጎን እንዳያዘነብል፤ ሚዛኑን እና ልኩን ጠብቆ እንዲቆም የሚያደርግ ነው። አዕማድ ስንልም ምሰሶዎች (ለብዙ) ማለት ነው ። ቤት በአምድ (በኮለም) እንደሚጸና ሃይማኖትም በእነዚህ አዕማደ ምሥጢራት ተጠቃሎ ይገለጻል፤ ምዕመናንም እነዚህን ምሥጢራት በመማር ጸንተው ይኖራሉ ።

ምሥጢር ማለት ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች ብቻ ተጠብቆ የሚቆይ ጉዳይ ሲሆን፤ አእማደ ምሥጢር ስንልም በሚታዩ ምሳሌዎች የማይታየውን የሃይማኖት ምሥጢር መረዳት፤ በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ ማግኘት ማለት ነው።

አምስቱ አእማደ ምሥጢር የምባሉት፡-
፩) ምሥጢረ ሥላሴ፡-የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የምንማርበት
፪) ምሥጢረ ሥጋዌ፡ የአምላክን ሰው መሆን የምንማርበት
፫) ምሥጢረ ጥምቀት፡ ስለ ዳግም መወለድ የምንማርበት
፬) ምሥጢረ ቁርባን፡ ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም የምንማርበት
፭) ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን፡ ስለ ዳግም ምጽዓት የምንማርበት ናቸው ።



አምስቱ አዕማደ ምሥጢር በአፈጻጸማቸው በሦስት ይከፈላሉ ።
፩) ምሥጢረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ አምነን የምንቀበላቸው፤
፪) ምሥጢረ ጥምቀትና ምሥጢረ ቁርባን አምነን የምንተገብረው፤
፫) ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን አምነን በተስፋ የምንጠብቀው።

እነዚህን ምሥጢራት በቅደም ተከተል እንመለከታለን፤

### ፩) ምሥጢረ ሥላሴ

ሠለሰ ሦስት አደረገ፤ ካለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ፤ ሥላሴ ማለት ሦስትነት ማለት ነው ። ምሥጢረ ሥላሴ ስንልም የአምላክን አንድነት እና ሦስትነት ማለታችን ነው።

ሥላሴ በስም፤ በአካል፤ በግብር ሦስት ናቸው ብንልም በመለኮት፤ በህልውና፤ በባሕርይ፤ በእዘዝ በአገዛዝ በመሳሰሉት አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ ተብሎ ይታመናል ይጠራል እንጅ ሦስት አማልክት አይባልም። ከዚህም የተነሣ ሥላሴ ሦስት ሲሆኑ አንድ፤ አንድ ሲሆኑ ሦስት በመሆናቸው ምሥጢር ተባለ። ይህም ለሚያምን ብቻ የሚገለጽ ምሥጢር ነዉ።

- በሥም፡- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ (ማቴ. ፳፰፡፲፱)
- በግብር፡- አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው። (ዮሐ. ፲፬፡፳፫)
- በአካል፡- ለአብ ፍጹም አካል፣ ለወልድ ፍጹም አካል፣ ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል አለው (ማቴ. ፫፡፲፯)

የምሥጢረ ሥላሴን ትምህርት የጀመረው ራሱ እግዚአብሔር ነው። መጀመሪያ አዳምን ሲፈጥረው ሰውን እንፍጠር በመልካችን እንደ ምሣሌያችን ብሏል (ዘፍ. ፩፡፳፮)። እነሆ በዚህ አንቀጽ “እንፍጠር በመልካችን እንደ ምሣሌያችን” የሚለው ንግግር የሁለት የሦስት ተናጋሪዎች እንጂ የአንድ ተናጋሪ ቃል አይደለም። በመቀጠል “እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም ከኛ እንደ አንዱ ሆነ” (ዘፍጥረት ፫፡፳፪)። ስለዚህ እግዚአብሔር ከኛ እንደ አንዱ ሆነ በማለቱ ሦስትነቱን ያስረዳል።

እግዚአብሔርም አለ “ኑ እንውረድ ቋንቋቸውንም እንደባልቀው አንዱ የባልንጀራውን ነገር እንዳይሰማ” ብሏልና። (ዘፍጥረት ፲፩፡፯) እነሆ በዚህ አንቀጽ እግዚአብሔር “ኑ እንውረድ” ብሎ በመናገሩ ከሁለትነት የተለየ ሦስትነትን ያስረዳል። መረጃውም ሦስት ተናጋሪዎች በአንድ ቦታ ሆነው ሲነጋገሩ ሦስተኛው ሁለቱን “ኑ እንውረድ” ሊላቸዉ ይችላል። ሁለት ሆነው ግን አንዱ ሁለተኛውን “ና እንውረድ” እንጂ “ኑ እንውረድ” ሊለዉ ስለማይችል ነዉ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ቃላት ተገልጸው ሲተረጎሙ አካላዊ ልባቻው አብ፤ አካላዊ ቃሉ ወልድ እና አካላዊ ሕይወቱ (እስትንፋሱ) መንፈስ ቅዱስን ሰውን እንፍጠር በመልካችን እንደ ምሳሌያችን ብሎ እንዳነጋገራቸዉ ይታወቃል።

የእግዚአብሔር የአንድነቱ እና የሦስትነቱ ማስረጃ ሁነው የታመኑ እነዚህ ሦስት ቃላት ከአንድ የበዙ ተናጋሪዎች ቃላት መሆናቸው ይታወቃል። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህም በሌላ አንቀጽ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን አይቶት እንዲህ ይላል፡- “ዖዝያን ንጉሥ በሞተበት ዓመት እኔ እግዚአብሔርን ከፍ ባለ በረጅም ዙፋን ተቀምጦ አየሁት፤ ሱራፌልም ከርሱ በላይ ቁመው ነበር። አንዱም ለአንዱ እንዲህ ሲሉ ይጮኹ ነበር፡- ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ ምድር ሁሉ ምስጋናውን ሞልታለች (ኢሳ. ፮፡፩-፫)።

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸውም” ሲል ራሱን አብን እና መንፈስ ቅዱስን በመግለጽ ከሦስት አካላት ያልበለጠ ከአንድ አካልነት የወጣ ከሦስት አካላት ያልበዛ ሦስት ብቻ መሆኑን አስረድቷል። (ዮሐ. ፲፫፡፳፮፤ ማቴ. ፳፰፡፲፱)።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣*

*ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!*

*በሊቀ ስዩማት ቀሲስ ዓለማየሁ አሰፋ*

# ነገረ ቅዱሳን

## “ወመልአከ እግዚአብሔር ዘአድኃነኒ እምኲሉ እኪት”
## (ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ፤ (ዘፍ. ፵፰፡፲፭)

እግዚአብሔር አምላክ መላእክትን እና የሰውን ልጆች ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ ፈጥሯቸዋል። ለዚህም ቅዱስ ዳዊት “ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈስ ወለክለ ይትለአክዎ ነደ እሳት” እንዲል (ዕብ. ፩፡፯)። ፈጥሯቸውም በሦስት ከተሞች በኢዮር፣ በራማ እና በኤረር አሰፈራቸው።

በኢዮር አርባውን ነገድ በማስፈር ለአራት ከፍሎ አጋእዝትን ኪሩቤልን ሱራፌልንና ኃይላትን አድርጓል፤ የኃይላትን አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን ሾሞታል “ሚካኤል ሥዩም በዲበ ኃይላት” እንዲል ኋላም በአጋእዝት ላይ አለቃ የነበረው ሰማልያል ሲወድቅ ቅዱስ ሚካኤል በአጋእዝት ላይ ሥልጣን ተቀዳጅቷል። “አሁን የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ መጥቻለሁ” እንዲል። (ኢያ. ፭፡፲፬)የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ስልጣኑ አለቅነቱ በእግዚ አብሔር ሠራዊት ሁሉ ላይ ታዳጊነቱ （እርዳታውም） ለሁሉም ፍጡር ነው። ይኸው እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ጎርፍ ፈሳሽ ሳይሆን የሕይወት መመሪያችን በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ዘፍ. ፵፰፡፲፮ ላይ እናገኘዋለን። “ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ” (ዘፍ. ፳፰፡፲፪) በማለት እንደተጻፈው በምድረ ሎዛ የመላእክትን የሰው ልጅ ልመና ወደ እግዚአብሔር ሲያደርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሰው ልጆች ሲያመጡ በመሰላል አምሳል ከፍቶ ትድግናቸውን አስቀምጦልናል። የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንዲይዙ የአብርሃምን የይስሐቅን የያዕቆብን የሃይማኖት መሪነት አደራ እንዲሸከሙ ለቀጣዩም ትውልድ እንዲያሸጋግሩ ሁለቱን የልጅ ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን ለኔ ይሁኑ ሌሎቹ ግን ላንተ ይሁኑ ካለ በኋላ በአመስቅሎ እድ የአባትነቱን ቡራኬ ከሰጠ በኋላ “ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ” በማለት የአባቶችን አደራ ለመረከብ የቅዱሳን መላእክት ጥበቃ እንደሚያስፈልግና በሕይወታችን በኑሮአችን ውስጥ ዕለት ዕለት መሆናቸውን የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳናል።

ነብየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም ሰይጣን እሥራኤልን እንዲቆጥር ባነሳሳው ጊዜ በዐውደ አርና ኢያቡሳዊት ዓይኑን አነሣ የእግዚአብሔር መልአክም በምድርና በሰማይ መካከል ቆሞ የተመዘዘ ሰይፉንም በእጁ ሆኖ ባየ ጊዜ በፊቱ በመስገድ መቅሰፍቱን እንዲያርቁ ለምኖታል፤ በዚያም መሥዋዕት አቅርቦ ተቀባይነት እንዳገኘ በአንደኛ ዜና ፳፩፡፲፮ ተጽፎ እናገኛለን።

እንዲሁም “በእውነት መጽሐፍ የተጻፈውን እነግርሃለሁ በዚህ ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር የሚረዳኝ የለም” (ዳን. ፲፡፳፩)። ታላቁ ነብይ ዳንኤል በእውነት ጽሑፉ የተጻፈውን እነግርሃለሁ በማለት የመጋቤ ብሉይ ተራዳኢ ቅዱስ ሚካኤል መሆኑን በማያሻማ መልኩ አስቀምጦልናል።

ወበእንተ ዝ ተገብረ ሎቱ በዓል ስለክብሩና ስለ አማላጅነቱ ወር በባተ በየአሥራ ሁለት ቀን መታሰቢያውን እንድናደርግ አዘዙን ከምን አግኝተው ቢሉ በመጽሐፈ መሳፍንት ፲፫፡፲፯-፲፱ እንዲህ የሚል ኃይለ ቃል እናገኛለን “ የእግዚአብሔር መልአክም ተአምር አደረገ ማኑሄም መልአኩን የነገረህን በደረሰ ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማን ይባላል ለምንት ትሴአል ስምየ ወመድምም ውእቱ” ብሎታል ማኑሄም የፍየል ጠቦት ወስዶ ለመሥዋዕት አቀረበ የእግዚአብሔር መልአክ ከመሠዊያው ነበልባል ጋር ወደ ሰማይ አረገ። ስሜም ድንቅ ነው “ ሚካኤል ብሂል ዕፁብ ነገር” እንዲል ደራሲ። በመሆኑም ዛሬም ለኛ በሚያደርግልን ተአምራት እናከብረዋለን ስእለታችን ሲደርስ ለቅዱስ ሚካኤል ነግሬው ነበረ ብለን ነገራችን በደረሰልን ጊዜ ስሙን እናነሳለን።

የቅዱስ ሚካኤል መታሰቢያኅዳር 12 እና ሰኔ 12 በታላቅ ድምቀት የሚከበርበት ነው። የሰኔ 12 ቀን የሚከበርበት ምክንያት አባ እለ እስክንድሮስ የተባለ አባት ሊቀ ጳጳሳት በሆነበት ወራት የግብፅ ንጉስ የበጥሊሞስ ልጅ ዙሐል የሚባል የኮከብ ጣዖት ሠራች “ወኮነ በውእቱ ምኩራብ ጣዖት ዘብርት” እንዲል በጣም ታላቅና በአውራጃው የገነነ ከ300 ዓመት በላይ የቆየ ወገብሩ ሎቱ በዓል አመ 12 ለወርኃ ሰኔ በዚያም አባ እለእስክንድሮስ ያንን የጣዖት ምኩራብ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመቀየር ማኑሄ መሥዋዕቱን ለእግዚአብሔር እንዳቀረበ ለጣዖት ይሠዋ የነበረ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር እንዲሆን በማድረግ የሊቀ መልአክት የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት አስገብቶ ቅዳሴ ቤቱን አክብረውበታል። ወተሠረዓ ዝንቱ በዓል እስከ ዛቲ ዕለት ይህ በዓል ሆኖ እስከ ዛሬ ተወሰነ።

በዚህች ቤተ ክርስቲያን በየወሩ የቅዱስ ሚካኤል ዝክር የሚያዘክሩ መታሰቢያውን የሚያደርጉ ወፈድፈደሰ በኅዳር ወበሰኔ ባልና ሚስት ነበሩ በጎረቤቱም ይህን ሥራቸውን የማይወድ ሀብታም ይኖር ነበር። ይህም በጎ ሰው ከብዙ ጊዜ በኋላ አረፈ ሚስቱም ፀንሳ ነበር በቅዱስ ሚካኤል አማላጅነት መልኩ በጣም ያማረ ልጅ ወለደች ቅዱስ ሚካኤል ሕፃኑን ባረከው እና የዚህን ንፉግ ባለፀጋ ሀብት እንዲወርስ አዝዟል ብሎ ሲናገር ያደምጥ ነበር። መልአኩን የተናገረውን ሰምቶ ሕፃኑ  አሥር ዓመት ሲሞላው በሳጥን አድርጎ ወደ ባሕር ወርውሮታል በሊቀ መልአኩ ታዳጊነት እሩቅ ሀገር አንድ በግ እረኛ አግኝቶት ስሙን ባሕራን ብሎ አሳድጎታል። ዮናስ በዓሣ ነባሪ ሆድ ሦስት ቀን ያሳደረ አምላክ ይህንንም ባሕራንን ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቆ ከዚያ አድርሶታልና ኋላም ይኸው ባለፀጋ ከነባሕራን ቤት በእንግድነት አድሮ የባሕራንን የስሙን ትርጉም ወራቱን ዓመታቱን ጠይቆ እሱ ወደ ባሕር የወረወረው መሆኑን በመረዳቱ ደብዳቤ በመጻፍ እንዲገድሉት “ቅትሎ ወግድፎ ውስተ ግብ” ብሎ ሰጥቶት ይህቺን የሞት ደብዳቤ ሊቀ መልአክ ለነማኑሄ በሰው አምሳል እንደተገለጠው ለባህራንም በንጉሥ ስፍራ አምሳል ተገልጦ ወደ ሕይወት ቀይሮለታል “እስመ አነ ወሀብክዎ ኮሎ ንዋይየ” በቤት ያለኝን ሁሉ ሰጥቸዋለሁ።

ባሕራንም የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያ ሲያደርግ ቀሲስ ሆኖ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግል ኖረ። ያን ጊዜ ማኑሄ የእግዚአብሔርን መልአክ መሆኑን አወቀ መሳ. ፲፫፡፳፩ እንዲል ባሕራን ከመንገድ ላይ የተገለጠለት የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤልን መሆኑን አወቀ።

በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወደ አዘጋጀሁልህ ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ መልአኬን በፊትህ እልካለሁ ስማው እምቢ አትበለው ስሜ በእርሱ ስለሆነ። ሁላችንንም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነን ወደ ተዘጋጀልን ሥፍራ እስክንገባ በክንፈ ረድኤቱ ይጠብቀን በአማላጅነቱና በተራዳኢነቱ እንማፀን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣*

*ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!*

*በቀሲስ በለጠ ጓሉ*

# የተባረከ ቤተሰብ

ማንኛውም ቤተሰብ ልጆቹ አድገው ጥሩ ደረጃ እንዲደርሱለት መልካም ምኞቱ ነው። ይሁንና ቤተሰብ እንደተመኘው ልጆች ሁሉ የቤተሰብን ፍላጎት ይዘው ያድጋሉ ማለት ግን ያስቸግራል። ለዚያም ነው አባቶች ሲመርቁ "የተባረከ ልጅ ይስጥህ" የሚሉት፤ እርግጥም ትልቅ ምርቃት ነው።

የተባረከ ልጅ ከሚለው ተነስቼ የዛሬ ጽሑፌን "የተባረክ ቤተሰብ" ብዬ ባቀርብ ማጋነን አይሆንብኝም። የዛሬ እንግዳዬ እነሆ ታዳጊ ወጣት እግዚእኃርያ ይልማ በቅፅል ስሟ (እኑዬ )በመባል ትታወቃለች።



የሊቀ መዘምራን ይልማ ኃይሉ እና የወ/ሮ ኂሩት ገዛኸኝ የበኵር ልጅ ነች። እኑዬ በይዘቱ የመጀመሪያ እና ልዩ የሆነ የአባቷን የሊቀ መዘምራን ይልማ ኃይሉን የአማርኛ መዝሙር በእንግሊዝኛ ይዛ የቀረበች ታዳጊ ወጣት ነች።

እርግጥ ነው የዚህችን ታዳጊ ሥራ ስናስብ ወዲያው ብልጭ የሚልብን ማናት? የማናት ልጅ? ቤተሰቦችዋ እነማን ናቸው? የሚለው ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። በእርግጥም ለዚህ ሥራ መሳካት ትልቅ ሚና የተጫወቱትን ቤተሰቦችዋን ለማግኘት ነው በቅድሚያ ያሰብነው።

እንደሚታወቀው ሊቀ መዘምራን ይልማ በአገልግሎት ሕይወቱ በጣም የተጠመደ በመሆኑ ምንም እንኳን ጥሪዬን ተቀብሎ ሊያነጋግረኝ ቢሞክርም በተለያዩ የፕሮግራም መደራረብ ምክንያት ሳንገናኝ ቀርቷል። ይሁንና የቤቱም፣ የውጪውም፣ የቤተ ክርስቲያኑም አገልግሎት አጠነከረኝ የምትለው ወ/ሮ ኂሩትን አግኝቼ ለማነጋገር እድሉን አግኝቻለሁ።

ትሁትና ሰው አክባሪ የሆኑት፣ ፍልቅልቅ፤ ሁሌም ፈገግታ የማይለይው የወ/ሮ ኂሩት ፊት አሁንም ድቅን ይልብኛል።

**ጥያቄ-** እንዬ አስተዳደግዋ እንዴት ነበር?

**ወ/ሮ ኂሩት** ለመመለስ አልተቻኮሉም ነበር፤ ቆዘም እንደማለት ብለው ደስ የሚል አዓናቸውን አንዴ ልጃቸውን አንዴ እኔን እያዩ ሰው ያለውን ነው የሚሰጠው እኔ ያለፍኩበትን ሕይወት ልጆቼ እንዲያልፉብት በጣም እፈልጋልሁ፤ እመኛለሁ። እንዬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ፍቅር ያደገች። ቅዳሴና ንግሥ በአላት ብቻ ሳይሆን፤ ማሕሌት እንዲያመልጣት የማትፈልግ፤ በልጅነት እድሜዋ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር አድሮባት በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያደገች ልጅ ናት።እንዬ እንደ ልጅ እንቅልፍ የማያታልላትና ብርድ የማይበግራት ፤ የሚኒሶታ ኔጋቲቭ ዲግሪ መቼም ጥያቄ ሆኖባት የማያውቅ ልጅ ናት ብል ማጋነን አይሁንብኝ። የ2:00 A.M ማሕሌት ለመካፈል የመቀስቅሻ ሰዓቷን ለ12፡00 A.M. ሞልታ ማንም ሳይቀሰቅሳት እራሷ በርትታ ሌሎቻችንን የምታበረታ፥ ታላቅ እኅት፣ ልጅ፣ እንደ መካሪም ፣ እናትም ሆና ያደገች ልጅ ነች። **ጥያቄ-** እዚህ ተወልዳ ካደገች አማርኛ ቋንቋ እንዴት አላስቸገራትም?

**ወ/ሮ ኂሩት-** ትምህርት ቤት ሲዘጋ/ summer time/ እቤት ውስጥ ያለ ምንም መሰላቸት እንደ አንድ ፕሮጀክት ወስጄ አማርኛ ዕለት ዕለት ከሁለቱ ወንድሞችዋ ጋር አስተምራቸው ነበር። ሌላው ራሱን የቻለ የቤተሰብ ጊዜ አለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አለን ያ የበለጠ አማርኛውንም የእግዚአብሔርንም ቃል ለመማማር ረድቶናል። ልጅ እያሉም ለሁለት ዓመት ያህል ኢትዮጵያ ሄደው ከአያታቸው ጋር ለትንሽ ጊዜም ቢሆን አሳልፈዋል።

**ጥያቄ-** እንዬ ባሕሪዋ እንዴት ነው?

**ወ/ሮ ኂሩት-** ይሄን ጥያቄ ስመልስ እውነትም ከልጄ ፊት ወይም እሷ በሌለችበት የምናገረው እውነታ ነው። እንዬ በቃ "እናት" ናት ብዬ ነው የምገልጻት። ሰው አክባሪ፣ ከሰው ተግባቢ፣ አፍቃሪ፣ አዛኝ፣ ለጋሽ፣ ረዳት፣ ለታናናሾቿ አርአያ የምትሆን፣ ለሰው ልጅ መልካም የምታስብና መልካም ሥነ-ምግባር ያላት ልጅ ነች። ይገርማል! እግዚአብሔር የባረካት እንዬ ይኼ ሁሉ ስለሷ ሲባል ምንም ድንቅም አላላትም ነብር። ይልቁንስ በሃሳብ እናቷን ለመርዳት ስትሞክር ግርም እያለኝ ነበር የማስተውላት። ወደሷ ዞር አልኩና፡-

**ጥያቄ-** እንዬ ይህንን ሥራ ለመሥራት ምን ነበር ያነሳሳሽ? መተርጎሙስ አላስቸገርሽም?

**እንዬ** - ፈጠን ባለና በሚጣፍጥ ጉራማይሌ እ ኖ! ኖ! ምንም አላስቸገረኝም።

ይህ ሥራ አዲስ አይደለም። ለሕዝብ ተሠርቶ አለመውጣቱ ነው እንጂ ከሠራሁት በጣም ቆይቻለሁ። ሲጀመር የአባቴን ካሴት መዝሙር ሰስማ ነው ያደኩት፤ ሲቀጥል ደግሞ ሁልጊዜ ከማዳመጤ የተነሳ ከቦታ ቦታ ስንሄድና ከወንድሞቼ ጋር መኪና ውስጥ ሆነን “ዜማው እንዲህ ቢሆንስ ምቱ እንደዚህ ቢቀየርስ፣ ቀጥተኛ የመዝሙሩን ትርጉም እየተረጎምን በእንግሊዝኛ እንደዚህ ብንዘምር” እያልን ቃላት እየቀያየርን እንዘምራለን። ልምዱና ፍላጎቱ ከዛ የመጣ ሲሆን ትርጉም ላይ ያለ ማጋነን ምንም አልተቸገርኩም ነበር።

ምክንያቱም እናቴና አባቴ ከጎኔ ናችውና። ለምጠይቀው ጥያቄ ሁሉ መልስ አገኛለሁ። ሌላው መጽሐፍትና መዝገበ ቃላት በጣም አገላብጣልሁ፤ አነባለሁ። የቤተ መጻሕፍት ቤትም ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል ለመረጃና ለትርጉም።

(ወደ ገጽ 8 ዞሯል)

## የሕፃናት እና ወጣቶች ዓምድ

### Enter Through the Narrow Gate (Mathew 7:13)

Over the years, I have seen our Orthodox Tewahedo children leave our church using the same doors they entered for several years. As first generation children, our church is struggling to maintain our youth within the faith let alone the church. As a congregation we are unaware or unwilling to accept the issues facing our youth growing up in America. We are not special; issues that are a difficult to any other young children affect us on a daily basis. Surprisingly, these issues are affecting kids at a younger and younger age. The only solution is for the church to teach the youth about the narrow gate and tell them how to enter. This mission was accomplished through United Orthodox Tewahedo Youth's 2nd Annual Conference: Enter Through the Narrow Gate (Mathew 7:13).

Alongside 160 guests (children and adults) from all over the United States, we learned about the narrow gate and what each of us must do to get through. Having attending all of the sermons on Saturday I was blown away and must share what I have learned with you. Deacon Dawit Muluneh gave a profound sermon on the narrow gate. He described the two roads: one is a wide road leading to destruction but is the road of comfort for the flesh and the other is the narrow road leading to salvation. Drawing on his own life experiences and the experiences of others, he grasped our attention and encouraged us to find the narrow road. Taking it a step further he had each of us write down what is one thing we would like to work on over the year and what spiritual step we will take to accomplish this. Watching an auditorium full of youth take part and write in their notes their goals and actions was very powerful.Deacon Ephrem Megenta and Kesis Sayefa gave powerful sermons on the "how" to travel the narrow road and enter the narrow gate. Deacon Epherem shared the 5 important pillars of living an orthodox life: liturgical life, fasting, contemplation of holy books, self-control, and living a life of charity. Kesis Sayefa, identified 5 rules of spiritual warfare: loving all people, using a spiritual eye, forgiving, not loving the world, and being doers of the world not just listeners. Attendees asked deep intellectual questions and received answers directly from the bible without judgment. Witnessing Zemari Yilma and Zemarit Fanut's children, Zemarit Egzihariya and Zemarit I am eternally grateful to those who thought of organizing the youth in such a way. I am thankful for the committee members, to TASK Sebeka Gubea and our fathers who worked hard to organize this conference this year. Seeing our own Sunday school members, who were once the young taking on the responsibility of playing host gave me hope? The unity our church congregation showed to make this conference successful was beautiful.

Attending this conference truly clarified many questions about my own spiritual journey. Although many argue the use of English as the primary language, it is important to realize we must meet our youth where they are. Their spiritual journey within our faith is crucial. We must not watch our children leave through the same church doors they entered all through their childhood. May God help and protect us all.

By Lelna Desta

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በጥያቄ እና መልስ

## መቋሚያ

ባለፈው ወር ጋዜጣችን በከበሮ የጀመርነውን የቅኔ ማሕሌት የዜማ መሣሪያዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ፤ ተምሳሌት እና ምሥጢር በመቀጠል በዚህ ወር መቋሚያን አስመልክቶ ጥያቄዎች ይኖሩናል።



**መቋሚያን አስመልክቶ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ!**

፩) መቋሚያን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመዝሙር የዜማ ማሣሪያነት ያዋለ ኢትዮጵያዊ ማነው?

፪) መቋሚያ የምን ምሳሌ ነው?

፫) የመቋሚያን ሥርዓተ ማሕሌት አጠቃቀም አስመልክቶ የሚከተሉትን ምሳሌያዊ ትርጉም/ምሥጢር ይግለጹ!

ሀ) መቋሚያን መጀመሪያ ከላይ ወደታች ማውረድ ከዚያም መቋሚያውን ከግራ ወደ ቀኝ ማሽከርከር፤

ለ) መቋምያን መሬት ላይ መደሰቅ ከዚያም ወደ መሬት የደሰቁትን መልሰው ወደ ላይ ማንሣት፡

ሐ) ከቀድሞ በበለጠ ከፍ ማድረግ ከዚያም ረጋ ብሎ መመለስ።

---

## በግንቦት ወር ጋዜጣችን ከበሮን አስመልክቶ ለቀረቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጥያቄዎች መልስ

### የከበሮ ክፍሎች ትርጉም/ምሥጢር

፩) ሰፊው የከበሮ ጎን ፡- የመለኮት ምሳሌ ሲሆን የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ምሉዕ በኲለሄ መሆኑን እና ስልጣኑም ወሰን ድንበር እንደሌለው ሊያስታውሰን ነው። የአፉን መስፋት ስንመለከት በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በህልውና ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተስተካከለ ሁሉን የያዘ ሁሉን የሚገዛ መሆኑን ለማሳሰብ ነው።

፪) ጠባቡ የከበሮ ጎን፡- የትስብእት ምሳሌ ነው በመዝሙር ጊዜ እየተቆረቆረ ድምጽ የሚሰጠው ጠባቡ የከበሮ ጎን የወልድ በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ መገለጥን የሚያመለክት ነው። ፍጥረታትን ሁሉ የሚገዛ እሱ በስልጣኑ ሽረት በመለኮቱ ኅልፈት የሌለበት ቢሆንም ሥጋን ተዋሕዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ተገልጧል።

፫) ከበሮ የሚለብሰው ጨርቅ/ ግምጃ፡- ከበሮ የጌታችን ምሳሌ እንደሆነ ከላይ አይተናል። ከዚህ አንጻር የለበሰው ጨርቅ ደግሞ በዕለተ ዓርብ አይሁድ ጌታችንን ያለበሱት ጨርቅ (ቀይ ከለሜዳ) ምሳሌ ነው። ለመዘባበቻ አይሁድ ሸፍነው "መኑ ጸፍዓከ ወመኑ ኮርአከ ተነበይ ለነ ክርስቶስ፡ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር።" ሉቃ. ፳፪፡፷፬ እያሉ የሸፈኑበት ግምጃ ምሳሌ ነው። "ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት" ማቴ. ፳፯፡፳፰

፬) ከበሮ ማሰሪያ ጠፍር፡-  በጌታችን ጀርባ ላይ የታየው የግርፋት ሰንበር ምሳሌ ነው። ጠፍሩን በከበሮው ላይ ስንመለከት በጌታችን ጀርባ ላይ የታየውን ሰንበር እናስታውሳለን። "እጆቼን እና እግሮቼን ቸነከሩኝ አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ" መዝ. ፳፩(፳፪)፡፲፯ እንዲል ጌታችን አጥንቱ እስኪቆጠር ጀርባው እስኪቆስልተገርፏልና የዚያ ምሳሌ ነው።

፭) የከበሮው ማንገቻ፡- ከበሮ ስንመታ አንገታችን ላይ የምናስገባው ማንገቻ ጌታችንን አስረው የጎተቱበት ገመድ ምሳሌ ነው። አይሁድ ጌታችንን ወደ ቀራንዮ ሲወስዱት የእጁ መጋፊያና መጋፊያ እስኪገጥም ድረስ በገመድ የእንግርግሪት አስረው ጎትተውታል ማገቻውን ከበሮው ላይ ስናይ ይኸንን ጌታችን የታሰረበትን ገመድ እናስታውሳለን።

፮) በከበሮ ውስጥ የሚደረጉ 3 ወይም 5 ጠጠሮች ፡- ሦስት ጠጠሮች ከሆኑ ምሥጢረ ሥላሴን አምስት ጠጠሮች ከሆኑ አምስቱን አዕማደ ምሥጢራትን ያስረዳል።

### የከበሮ አጠቃቀም ምሳሌያዊ ትርጉም/ምሥጢር!

፩) ከበሮ ግራና ቀኝ መመታቱ፡-"ዘበእንቲአሃ ለቤተክርስቲያን ተጻፋእከ በውስተ ዓውድ ከመትቀድሳ" ያለውን በማስታወስ የግራና የቀኝ ጉንጩ ምሳሌ ነው።

፪) መዘምራን ግራና ቀኝ እያሸበሸቡ  ከበሮ መምታታቸው፡- ይህ የሚያሳየዉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ቀያፋ፣ ከቀያፋ ወደ ጲላጦስ ያደረገው እንግልት ነው።

፫) ከበሮ መጀመሪያ በርጋታ መመታቱ ከዚያም በፍጥነት መዘዋወሩ፡- ይህ ምሳሌነቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ እንደያዙት መጀመሪያ በቀስታ እየዘበቱ እንደመቱት፣ በኋላም ጲላጦስ ተመራምሮ ነፃ ሳያወጣው፣ የሰንበት ቀን ሳይገባብን ኑ እንደብድበው የማለታቸው ምሳሌ ነው ።

፬) በማሕሌት ላይ ከበሮ መሬት ላይ ተቀምጦ መመታቱ፡- ምሳሌነቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሬት ላይ ወድቆ መንገላታቱን ለማሳሰብ ነዉ።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣*

*ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!*

*በዶ/ር ስሎሞን ፎሌ*

# ቅዱሳት ሥዕላት

## ፩- የቅዱሳት ሥዕላት ትርጉም፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት እና ትውፊት ቅዱሳት ሥዕላት ማለት፤ በአብያተ ክርስቲያናት ግድግዳ፡ በሸራ፡ በብራና፡ በወረቀት እና በመስቀሎች ላይ በቀለም ወይም በጭረት ባለ ሁለት ጎን (two dimensional) ሆነው የሚሣሩ የልዑል እግዚአብሔርን፡ የእመቤታችንን፡ የቅዱሳን መላዕክትን፡ የጻድቃንን እና የሰማዕታትን ማንነት የሚገልጥ መንፈሳዊ ጥበብ ነው። ሥጋዊውን ዓለም ከሚያንጸባርቁ መንፈሳዊ መልዕክት ከሌላቸው ሌሎች ሥዕላት ፈጽመው ስለሚለዩ ቅዱሳን ሥዕላት ይባላሉ።

## ፪- የቅዱሳት ሥዕላት አመጣጥ፤

### ፪-፩ በብሉይ ኪዳን

ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለያዘው ቦታ መሠረቱ የሁሉ አስገኝ የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር አስቀድሞ ለነቢዩ ሙሴ ሥዕለ ኪሩብን በሥርየት መክደኛው ታቦት ላይ እንዲያዘጋጅ ማዘዙ ነው። ለዚህም መሠረት በዘጸ. ም. ፳፭፡ቁ ፳፪ "በዚያም ካንተ ጋር እገናኛለሁ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ አነጋግርሃለሁ" ብሎ መናገሩ ነው። እግዚአብሔርም የተናገረውን የማያስቀር ነውና ሊቀ ነቢያት ሙሴን በሥዕለ ኪሩብ መካከል ሆኖ ድምጹን አሰምቶታል።

### ፪-፪ በሐዲስ ኪዳን

ከሐዋርያዊ ተልዕኮውና የሕክምና ሞያው በተጨማሪ የሥዕል ጠቢብ የነበረው ቅዱስ ሉቃስም ምስለ ፍቁር ወልዳን (እመቤታችን ከልጇ ከወዳጇ ጋር ሆና) በመሳል ለትውልድ አቆይቶልናል። በተጨማሪም ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ለጢባርዮስ ቄሳር የጌታችንን ሥነ-ስቅለት ሥዕል አዘጋጅቶ ሰጥቶታል።

## ፫- ቅዱሳት ሥዕላት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ ፊደል፡ ሥነ ጽሁፍ፡ ዜማ፡ ኪነ ህንፃ... ወዘተ እንዳሏት ሁሉ የራሷ የሆነ የሥነ ሥዕል ጥበብም ያላት ስንዱ እመቤት ናት። ከጥንተ ክርስትና የአክሱማውያን ዘመን ጀምሮ ሥዕል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቦታ እንደነበረው የአርኪዮሎጂ ግኝቶችና የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ፍርስራሾች ያመለክታሉ። በተለይ በዘመነ አክሱም ተሠርተው በከፊል የፈረሱ እና ከመፍረስ የተረፉ እንደ አብርሃ ወአጽብሐ፡ ውቅሮ ቅዱስ ቂርቆስ፡ ደብረ ዳሞ ገዳም፡ መርጡለ ማርያም፡ ወዘተ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የያዟቸው ሥዕሎች የዘመኑን የሥዕል ጥበብ አሻራ ያሳያሉ። በተለይ በመካከለኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ጥበብ ያደገበት ዘመን ነበር። በአሁኑ ወቅት በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት የምናገኛቸው ሥዕላት በዚህ ዘመን የተሠሩ ናቸው።

## ፬- የቅዱሳት ሥዕላት ጥቅም፡

### ፬-፩ ለሥርዓተ አምልኮ

ቅዱሳት ሥዕላት ሰውንና እግዚአብሔርን የሚያገናኙ መንፈሳዊ ሀብቶች ናቸው። በሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ፡ ወይንም መስገድ ሥዕሉን አምላክ ማድረግ አይደለም። ነገር ግን የሥዕሉን ባለቤት በሥዕሉ ፊት ሆኖ በመማጸን በረከቱን ለማግኘት የሚፈጸም ሥርዓት ነው። ሥዕሉ ለባለቤቱ መታሰቢያ ነው። "የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው ተብሎ እንደተጻፈ" ምሳ. ፲፡፯ የሥዕሉን ባለቤት አቅርቦ ያሳየናል። ገድሉን፣ ተአምራቱንና ቃል ኪዳኑን ያስታውሰናል። በመንፈስም ድልድይ ሆኖ ከሥዕሉ ባለቤት ያገናኘናል።

ሙሴና አሮን ወደ ደብተራ ኦሪት ገብተው በታቦቱና ሥዕለ ኪሩብ ፊት እየሰገዱ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ይቀበሉ ነበር ዘኁ. ፲፪፡፵፫

### ፬-፪ ለትምህርት

ቅዱሳት ሥዕላት ሲሣሉ የሥዕሉን ባለቤት ዐቢይ ገድልና ተአምራት በሚያጎላ መልኩ ነው። ስለሆነም ማንኛውም ምእመን የሥዕሉን ባለቤት መንፈሳዊ ተጋድሎ በቀላሉ እንዲረዳ ያደርገዋል። ለምሳሌ የጻድቁ አባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥዕል ሲሣል ለ22 ዓመታት 8 ጦሮችን ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ አስተክለው ሲጸልዩ አንድ እግራቸው በቁመት ብዛት መቆረጡን እንዲሁም ስለ ቅድስናቸው ከተሰጣቸው ስድስት የብርሃን ክንፎች ጋር ተደርጎ ይሣላል። ክህነታቸውን ለመግለጽም የእርፍ መስቀልና ጽና ይዘው ይሣላል። የሥዕሉ ባለቤት እንዲታወቅም በሥዕሉ ላይ አጭር የጽሑፍ መግለጫ ይቀመጣል። "ዘከመ ጸለየ አቡነ ተክለሃይማኖት" እንዲል። በዚህ ሥዕል ምእመናን የጻድቁን ተጋድሎ ይማሩበታል፤ አርአያም ያደርጉታል።

እንግዲህ ቅዱሳት ሥዕላት ይህን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡን ከሆነ በጥንቃቄ በመያዝ መገልገል እንደሚገባና ዘወትር በጸሎት ሰዓት ከፊት ለፊታችን በማስቀመጥ ልንጸልይ እንደሚገባ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መልዕክቷን ታስተላልፋለች።

ረድኤት እግዚአብሔር አይለየን!
በአቶ ፍቃዱ ቸሩ።

ከገጽ 4 የዞረ . . . . . . .**የተባረከ ቤተሰብ**

በተቻለኝ አቅም የአባቴን የአዘማመር style ለመከተል ሞክሬያለሁ። አንዳንድ ጊዜ ግን ከአማርኛ ቀጥታ ወደ እንግሊዘኛ ለመቀየር የሚያስቸግሩትን ዜማዎች እኔን በተመቸኝ መልኩ አድርጌ አቅርቤዋለሁ።

**ጥያቄ-** ካሴት ሲዲውን ከማውጣትሽ በፊትና በኋላ ያለው የሰው አመለካከትና ግንዛቤ እንዴት ነው? ያስተዋልሽው ነገር ካለ? ድጋፍ ወይም ማስተካከያ የሰጠሽ አለ?

**እንዬ-** እውነት እውነት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጠበቅ የሚወድ፣ ሥርዓቱ የተጓደለ ሲመስለው የሚቆጣን ኅብረተሰብ እንዳስተውል አድርጎኛል። ባጋጣሚ ሲዲው ከመታተሙ በፊት ለሲዲው የሽፋን ሰእል አስበነው የነበረው አሁን ካለው የተለየ ነበር። ይኸውም ባጋጣሚዎች አለመመቻቸትና በነገሮች አለመስተካከል ያሰብነው ሳይሆን ያልታሰበው ምስል የሽፋን ሰእል ሆኖ ወጣ።

በአጋጣሚ ተነስቸው የነበረ የኔ ፎቶ ሲሆን ይህ ፎቶ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት ላይ ሆኜ ያለ ምስል አልነበረም፤ ነገር ግን ይህ ፎቶ ብዙዎችን ጥያቄ አስነስቶባቸዋል። እኔ ግን የሰማሁዋቸውን ሐሳቦች ሁሉ "እውነት ነው ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከማሰባቸው ነው" ብዬ ጠቃሚነቱን ተቀብዬ አልፌዋለሁ። ግን በሥርዓት በኩል እግዚአብሔር ይመስገን  ሁሉንም ጠንቅቄ አውቃለሁ እናትና አባቴ ምስጋና ይግባቸው።

ከትምህርት ሰጪነቱ ጎን አያይዞ ደግሞ እዚህ ሀገር የተወለዱ አንዳንድ ሕፃናትና ወጣቶች መዝሙር ሲዘምሩ ትርጉሙ ሳይገባቸው ነበር የሚያልፉት አሁን ግን ደስ ብሏቸው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ትርጉሙ ገብቷቸው ሲዘምሩ ስሰማ ውስጤን ደስ ይለዋል።

ብዙዎች "THANK YOU ደስ ብሎናል" ያሉኝም አሉ። ካሴቱ በብዙዎች  ተደማጭ ነው ለሌሎች መማሪያ፣ አማርኛ ለማይናገሩ ግን ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዝሙር ማወቅ ለሚፈልጉ ትልቅ አስተማሪ ሆኖ አግኝቼዋለሁና እግዚአብሔር ይመስገን።

**ጥያቄ-** ከዚህ ጋር በተያያዘ ምን እየሠራሽ ነው ለመሥራትስ የምታስቢው ነገር ካለ?

**እንዬ-** ዲዛይን ማድረግ አርት ነገር በጣም ደስ ይለኛል ከዚህ ቀደምም የሠራኋቸው ዲዛይን ሥራዎች አሉኝ፤ በምኖርበት ካውንቲ አርት ሴንተር ውስጥ ለሕዝብ ዕይታ ቀርቧል። ወደፊትም በዛ መቀጠሉን እፈልጋለሁ።
ሌላው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቤተስብ የሌላቸውንና እርዳታ ለሚፈልጉ ሕፃናት እርዳታ ማድረግ እወዳለሁ።

ከዚህ በፊት ከምማርበት ትምህርት ቤት አስተባብሬ በአዲስ አበባ የሚገኙ




በአራዳ ክፍለ ከተማ ትምህርት ቤት ውስጥ ታዳጊ ሕፃናትን በቁሳቁስና በሚያስፈልጋቸው ረድቻለሁ። እሱንም ቀጣይ የሚሆንበትን መንገድ ወደፊት ለመቀጠል አስባለሁ። በወጣትነቴ ብዙ መሥራት አስባለሁ፤ በእኔ መጠቀም የሚችሉ ካሉ መጥቀም እፈልጋለሁ። ከሁሉ በበለጠ እግዚአብሔርን ለማገልገል እፈልጋለሁ "ALL ABOUT GOD" ወንድሞቼን፣ እናትና አባቴን በጣም እወዳቸዋለሁ፤ አመስግናቸዋለሁ። በሁሉ ነገር ስለሚረዱኝ በበለጠ ደግሞ እናቴ (MY BEST FRIEND) አሰልጣኜ፣ አማካሪዬ፣ ጓደኛዬ ነች። አባቴም HE IS MY ROLE MODEL በጣም እወደዋለሁ ብላለች።
እውነት ለመናገር ከዚህ የተከበረ ቤተሰብ ጋር የነበረኝ የሁለት ሰዓት ቆይታ ቃለ መጠይቅ ሳይሆን አንድ የሥነ-ምግባር አጭር ኮርስ የምወስድ ያህል ነው የተሰማኝ። ቆይታችን ልዩ በተመስጦ ልብ የሚማርክ ከመሆኑ አንዳንድ ጊዜ ሳላስበው የእንባ ዘላላዎች ሳብስ አገኘው ነበር እራሴን። እውነት ለመናገር ወደፊት ሰፋ ባለ መድረክ ይኼን ቃለ መጠይቅ ይዤ ለመቅረብ ቃል እገባለሁ። በቦታ እጥረት ብዙ ቆርጠናልና። ስለ እንዬ ወንድሞች ኢያቄምና ይኩኑ አምላክ ራሱን የቻለ አንድ ወጥ ጽሑፍ አለኝና።

እውነት ይህ ቤተሰብ በተለየ መልኩ እግዚአብሔርን ሲያገለግል እግዚአብሔርም ይህን ቤት እየባረከ እና እያገለገለ እንዳለ በፍጹም መገመት አያዳግትም። ከፍ ያለ ምስጋና ለወ/ሮ ኂሩት ገዛኸኝ፣ ለሊቀ መዝምራን ይልማ ኃይሉ ከሄደበት ከኖርዌይ ድረስ እየደወለ በማናገር ለረዳኝ፣ ልዩ የሆነ ሥራ ይዛልን ለቀረበችው ታዳጊ ወጣት እግዚእኃርያ ይልማ ታላቅ አክብሮቴን አቀርባለሁ።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር፣ ወለወላዲቱ ድንግል፣*

*ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን!*

*በወ/ት ዘመናይ ዘሪሁን*

